## የተሰውትንና በየጉድጓድ እስርቤቱ እየማቀቁ ያሉ ጀግኖቻችን አንርሳ! ቃል አናፍርስ!

### ታምራት ግዛቸውና ጓደኞቹ በወያኔ እጅ ከወደቁ 10 አመታቸው !! ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም.



ታምራት ግዛቸው በ1988ዓ.ም መጨርሻ ላይ የትጥቅ እንቅሳሴ ጀምሮ የነበረው የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ጀማሪ የሽምቅ ጦር የፖለቲካ ሃላፊ የነበረና ሃምሌ 19 ቀን 1989 ዓ.ም  በከሃዲ ጥቆማ ከሻለቃ አዱኛ አደመ ጋር በወያኔ እጅ የወደቀ የኢሕአፓ ነባርና ጠንካራ ታጋይ ነው። ታምራትና ሻለቃ አዱኛ በወያኔ እጅ ከወደቁ በኋላ መጀመሪያ ወደ መርትራድ ከዚያም ወደ ባህርዳር ከተወሰዱ በኋላ ደብዛቸው ጠፍቷል። በኢአግ እንቅስቃሴ ወቅት መዳረሻቸው ከጠፉት ውስጥ ደግሞ መአዛ፤ ፈይሰል፤ ሀይለ ሚካኤል (ሁሉም የትግል ስሞች)፤ታደለ መንገሻ ና ድንቁ ሺፈራው ይገኙባቸዋል።

ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች በመላ አገሪቱ በሚገኙ የጉድጓድ እስርቤቶ እየተሰቃዩ ነው። ታምራትና ሻለቃ አዱኛም ልክ እንደ ሌሎቹ በወያኔ እጅ እንደወደቁት የኢሕ አፓ ታጋዮች እንደ ጸጋየ ገብረመድህን( ደብተራው) ፤ ይስሃቅ፤ ህጎስ በዛብህ፤ ተሰፋየ ከበደ፤ ለማ ሀይሉ፤ ተክላይ ገ/ስላሴ፤ ደሳለኝ አምሳሉ፤ አበራሽ በርታ እና ሌሎችም አያሌ ታጋዮች ሁሉ በነዚህ እስርቤቶ እየተሰቃዩ እንደሆነ ይገመታል።

በረጅሙ የትግል ጉዞ የተሰውትና በወያኔ መዳፍ ስር ወቀው እየማቀቁ ያሉ ታጋዮች ለቀረነው ታጋዮች የሰጡት አደራ ቢኖር ህዝብ የስልጣን ባለቤት እስኪሆን ድረስ አብረን የጀመርነውን ትግል መቀጠልና ዳር ማድረስ ነው። የቀረነው ታጋዮች ባንዱ ወይም በሌላው ምክንያት ቀበቶችንን ብናላላ ቃል እንዳፈርስን፤ እንደ ክህደትም ይቆጠራል።

በሌላ በኩል

ሉዓላዊነቷ የተጠበቀና የፍትህ የበላይነት ለነገሰባት ኢትዮጵያ የሚታገሉ ሃይሎች ሁሉ ብረት አንስተው ሆነ በሰላም ወያኔን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለማወረድ በተደረገውና እየተደረገ ባለው ትንቅንቅ ለተሰው ታጋዮች ክብር ሊሰጡ፤ በየጉድጓድ እስር ቤቶች እየተሰቃዩ ያሉት ሁኔታ እንዲታወቅና እንዲፈቱ መጠየቅ መጀመር ይጠበቅባቸዋል። ትግሉ የ1997ቱ አይነቱ ህዝባዊ መነሳሳት ደረጃ ላይ ለመድረሱና ኢትዮጵያም ወያኔና ሻቢያ እንደተመኞት አለመፈረካከሷ ከሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች ድርና ማግ የተሰሩ ታጋዮች ባበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ጭምር መሆኑን ማስተዋል ያሻቸዋል።

ስየ አብርሃምና ጓደኞቹም እነጸጋየ ደብተራውና እነታምራትን ወያኔ ምን እንዳደረጋቸው እንዲነግሩን ልንጠይቃቸው ይገባል።

ትግሉ ይቀጥላል
ከትግል ጓደቻቸው
ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም.